## <u>ፍትህ የማግኘት መብት ማለት ምንድነው?</u>

ፍትህ የማግኘት መብት ማለት ዜጐች መደበኛ ወይም መደበኛ ያልሆነ የፍትህ ሥርዓትን ተጠቅመው በብሄራዊ እና በዓለም አቀፍ ሕጐች የተረጋገጡላቸውን ሰብአዊ መብቶች የሚያስከብሩበት መብት ነው።

## 1. <u>ፍትህ የማግኘት መብት ከዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች አንፃር</u>

ማንኛውም ሰው ፍትህ የማግኘት መብት እንዳለው ከሚገልፁት የዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሰነዶች ውስጥ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች የቃል ኪዳን ስምምነት ዋነኛው ነው። በዚህ የቃል ኪዳን ሰነድ ፍትህ ከማግኘት መብት አንፃር ከተደነገጉት ውስጥ፣

- ◊ ማንኛውም ሰው በፍርድ ቤቶችና በዳኝነት አካላት ፊት በእኩልነት የመታየት፣
- ◊ ማንኛውም ሰው የቀረበበት የወንጀል ክስ በሚሰማበት ጊዜ በህግ በተቋቋመ፣ ስልጣን ባለው፣ ነፃና ገለልተኛ በሆነ የዳኝነት አካል ዘንድ ተገቢ በሆነ ጊዜ የመቅረብና አድልኦ የሌለበትና ግልፅ የሆነ ዳኝነት የማግኘት፣
- ◊ ማንኛውም ሰው በሚያዝበት ጊዜ የተያዘበትን ምክንያትና የቀረበበትን ክስ በዝርዝርና ወዲያውኑ በሚገባው ቋንቋ የማወቅ፣
- ◊ በወንጀል ክስ የተያዘ ወይም የታሰረ ሰው ከዳኛ ወይም በህግ ስልጣን ከተሰጠው አካል ዘንድ በአፋጣኝ የመቅረብና ተገቢ በሆነ ጊዜ ውስጥም ዳኝነት የማግኘት ወይም የመለቀቅ፣
- ◊ ያለአግባብ በመታሰሩ ወይም በመያዙ ምክንያት ነፃነቱን የተነፈገ ማንኛውም ሰው በተገቢው የጊዜ ገደብ ውስጥ ፍርድ ቤት እንዲቀርብ ካልተደረገ ፍርድ ቤቱ የአካል ነፃነቱን እንዲያስከብርለት ጉዳዩን የማቅረብ፣
- ◊ ለቀረበበት ክስ መከላከያ ለማዘጋጀት አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች በቂ ጊዜ የማግኘትና አማካሪ እንዲሆን የመረጠውን ሰው የማማከር፣
- ◊ ራሱ በተገኘበት የመዳኘት፣ በግል ወይም በመረጠው ጠበቃ በኩል ራሱን የመከላከል፣ ጠበቃ ከሌለው የህግ አማካሪ እርዳታን የማግኘት መብት እንዳለው የማወቅ፣ ትክክለኛ ዳኝነት የሚጓደል ሆኖ ሲታይና የገንዘብ አቅሙ የማይፈቅድ ሲሆን ሳይከፍል ጠበቃ እንዲቆምለት የማስደረግ መብት ይገኙበታል።

በሌላ በኩል ደግሞ የቃል ኪዳን ሰነዱ አባል አገራት የሰዎችን ፍትህ የማግኘት መብት የማክበርና የማስከበር ግዴታ የተ ጣለባቸው ሲሆን በአንቀጽ 2/3/ ላይ ከተጠቀሱት ዋና ዋና ግዴታ ዎቻቸው ውስጥ የሚከተሉት ናቸው።፣

- ◊ ማንኛውም ሰው በቃል ኪዳን ሰነዱ እውቅና ያገኙት መብቶቹና ነፃነቶቹ በማንም አካል ቢጣሱበት ለደረሰበት በደል ውጤታማ መፍትሄ እንዲያገኝ የማረጋገጥ፣
- ◊ ለደረሰበት በደል መፍትሄ የሚሻ ማንኛውም ሰው ሥልጣን ባለው የፍትህ፣ የአስተዳደር ወይም የህግ አውጪ አካል፣ ወይም በአገሪቱ የህግ ሥርአት መሰረት ሥልጣን በተሰጠው ሌላ አካል መብቱ እንዲረጋገጥለት ለማድረግና ፍትህ እንዲያገኝ የማመቻቸት፣
- ◊ ሥልጣን ባላቸው አካላት የፍትህ ውሳኔ ሲሰጥ ይህንኑ የማስፈፀም ሀላፊነት እንዳለባቸው ተገልጿል።

ከላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ጽንሰ ሀሳብም በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 19፣ 20፣ 25 እና 37 ላይ የተገለፀ ጉዳይ ነው።

## 2. <u>የፍትህ ተቋማት</u>

ፍትሕ የማግኘት መብት በተሟላ ሁኔታ እንዲረጋገጥ የዜጐችን መሠረታዊ መብቶች የሚያስጠብቅ የሕግ ማዕቀፍ እና እነዚህን በሕግ የተረጋገጡ መብቶችን የሚያስከብሩ የፍትህ ተቋማት መኖርን የግድ ይላል። በአጠቃላይ ዜጐች በሕግ የተረጋገጠ መብቶቻቸውን ለማስከበር፣

- ◊ የመብቶች ባለቤት መሆናቸውንና መብቶቹ በሚጓደሉበት ወይም አደጋ ላይ በሚወድቁበት ጊዜ የት ሄደው መጠየቅ እንዳለባቸው የማወቅ፣
- ◊ መብቶቹን ለማስከበር የተቋቋሙና ሕዝቡ በቀላሉ ሊገለገልባቸው የሚችልባቸው የፍትሕ አካላትን ወይም ሌላ መፍትሄ ሰጪ ተቋማትን አሠራር ማወቅ፣

ነገር ግን ሁሉም ሰው በእኩል ደረጃ ሊጠቀምበት የሚችል ፍትህ የማግኘት መብትን የሚመለከት ሕግ ማውጣትና ተቋማትን መመስረት ብቻ በቂ ባለመሆኑ ከዚህ በተጨማሪ፣

- ◊ የፍትሕ ተቋማቱ ደረጃውን የጠበቀ ግልጋሎት የሚሰጡ መሆናቸውን፣
- ◊ ሕዝቡ ተቋማቱን በቀላሉና በመተማመን ሊጠቀምባቸው መቻሉንና፣
- ◊ የመብቱ ተጠቃሚዎች ስለመብታቸውና መብቶቹን ለማስከበር ስለተቋቋሙት ተቋማት በቂ ግንዛቤና እምነት ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

***የፍትህ ተቋማት በዋነኛነት መደበኛ እና መደበኛ ያልሆኑ ተብለው በሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ።***

### <u>መደበኛ የፍትሕ ተቋማት</u>

ፍርድ ቤትን፣ አቃቤ ሕግንና የፖሊስ ተቋማትን ጨምሮ መደበኛ የሚባሉት የፍትህ ተቋማት በሕግ አውጪው አካል በወጣ ሕግ መሰረት ስልጣን ተሰጥቷቸው የዳኝነትና ፍትሕ ነክ ጉዳዮችን በማየት በዜጐች መብትና ግዴታ ላይ ውሳኔ የሚሰጡ አካላት ናቸው። እነዚህ ሶስት ተቋማት በመደበኛ የፍትሕ ተቋማት ምድብ ውስጥ ትልቅ ሥፍራ ያላቸው ቢሆንም ከእነርሱ በተ ጨማሪ በዜጐች መብትና ግዴታ ላይ ውሳኔ ሊሰጡ የሚችሉ በርካታ አስተዳደራዊ መስሪያ ቤቶች እንዳሉ መገንዘብ ያስፈልጋል። ለምሳሌ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን፣ የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም፣ የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ፣ የአስተዳደር ፍርድ ቤቶች፣ ግብር ይግባኝ ኮሚሽን፣ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ፣ ማረሚያ ቤትና የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የሚጠቀሱ ሲሆን እነዚህ በሃገራችን ያሉና በመደበኛ የፍትህ ተቋማት ምድብ ውስጥ የሚካተቱ ናቸው።

### <u>መደበኛ ያልሆኑ የፍትህ ተቋማት</u>

መደበኛ ከሆኑትና በሕግ ሥልጣን ከተሰጣቸው ተቋማት በተ ጨማሪ የኅብረተሰቡን ባሕል መሰረት አድርገው በማኅበረሰቡ የሚቋቋሙ ባሕላዊ የዳኝነት አካላት፣ በባለሙያዎች የሚቋቋሙ ነፃ የሕግ ድጋፍ መስጫ ማዕከላት፣ በተከራካሪ ወገኖች ፍላጐትና ስምምነት የሚመሰረቱ የግልግል ወይም የእርቅ መድረኮች ፍትሕ በመስጠት ሂደት ውስጥ ትርጉም ያለው አስተዋጽኦ ያበረክታሉ። ለምሳሌ ያህልም ሽምግልና፣ ግልግልና እርቅ፣ ነፃ የሕግ ድጋፍ መስጫ ማዕከላት በአገራችን ካሉት መደበኛ ካልሆኑት የፍትህ ተ ቋማት ውስጥ የሚጠቀሱት ናቸው።

## 3. <u>ፍትህ የማግኘት መብትና በዝቅተኛ ኑሮ የሚኖሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች</u>

ፍትህ የማግኘት መብት ለሁሉም ዜጋ በእኩልነት ሊረጋገጥ የሚገባው መብት ነው። ይሁን እንጂ ይህን መብት ተግባራዊ በማድረግ ሂደት በድህነት ወይም በተለያዩ ምክንያቶች በሕግ የተ ሰጧቸውን መብቶች እውን ለማድረግ ያልቻሉ የሕብረተሰብ ክፍሎች በተቋማቱ እንዳይጠቀሙ የሚያደርጓቸው በርካታ ምክንያቶች አሉ። እነዚህም:-

### ሀ. <u>በህግ መሰረት ለመጠቀም ፍላጐት መቀነስ</u>

በዝቅተኛ ኑሮ ደረጃ ያሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች በሚከተሉት ዋና ዋና ምክንያቶች መብታቸውን ለማስጠበቅም ይሁን ግዴታቸውን ለመወጣት የተዘረጉትን የህግ ሥርአቶች መከተል አይፈልጉም።

- ◊ በህግ አለማመን (mistrust of law) እና በህገወጥነት አኗኗር ሁኔታ የመኖር ዝንባሌ (linking in illegality)
- ◊ የፍትህ ተቋማቱ የሚጠቀሙባቸውን ባዕድ የህግ ቃላቶች (alien idioms of the law) እና የአሰራር ስርአቶች አለማወቅ፣
- ◊ መሰረታዊ የህግ እውቀት አለመኖር፣ የፍትህ ተቋማትን አሰራር ለማወቅ የሚያግዝ መረጃ በበቂ ሁኔታ አለመኖር፣ተ ቋማቱ የሚጠይቁትን የአነጋገር፣ የአለባበስ፣ የአረማመድ፣ የአቀማመጥ፣ የክብር አሰጣጥና ሌሎች ስርአቶች ባለመጠበቅ ምክንያት የሚከተለውን ውጤት በማሰብ ኅብረተሰቡ በተ

ለይም ድሃው የኅብረተሰብ ክፍል ተቋማቱን በሚገባ በልበሙሉነት አለመጠቀም::

### ሰ. <u>በሕግ ባለሙያ /ጠበቃ/ የመታገዝ እድል አለማግኘት</u>

በፍትህ ተቋማት ወይም በአስተዳደር መስሪያ ቤቶች የሚደረጉ የህግ ክርክሮች የህግ ባለሙያ ድጋፍ መጠየቃቸው የግድ ነው:: ነገር ግን አብዛኛው ድሃ ኅብረተሰብ ባለበት የአቅም ማነስ ምክንያት የህግ ክርክሩን የሚያካሂደው በባለሙያ ሳይታገዝ ነው:: የባለሙያ እገዛ እንደሚያስፈልግ ግንዛቤው ቢኖረው እንኳ የባለሙያዎቹ የአገልግሎት ክፍያ ከኅብረተሰቡ አቅም በላይ ስለሚሆን ሳይጠቀምባቸው ይቀራል:: በዚህ ምክንያት በተለይ ከባለሙያዎች የሚጠየቀውን ከፍተኛ የአገልግሎት ክፍያ መሸፈን የማይችሉት ድሃ የኅብረተሰብ ክፍሎች የተሟላ ፍትህ የማግኘት መብታቸው በእጅጉ ይጐዳል::

### ሐ. <u>የፍትሕ መዘግየት</u>

በአብዛኛው የህግ ክርክሮች ረዥም ጊዜ ይወስዳሉ:: የዘገየ ፍትህ ደግሞ እንደተነፈገ ይቆጠራል:: በዚህም ምክንያት በዝቅተኛ ኑሮ የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች በህግ የተሰጧቸውን መብቶች ለመጠቀም አይበረታቱም::

## 4. <u>የመፍትሄ ሃሳቦች</u>

◊ ዜጐች በሕግ እንዲተማመኑና በሕገወጥነት እንዳይኖሩ ሥለ ሕጉ በቂ ግንዛቤ መስጠት፣
◊ የፍትህ ተቋማቱ ማንኛውም ሰው ሊረዳው በሚችለው ቋንቋ መጠቀም፣
◊ የፍትህ ተቋማቱ በተለይ ፍርድ ቤቶች አሰራራቸውንና ስለሥራቸው የሚያስረዱ መረጃዎችን ለህብረተሰቡ ማዳረስ፣
◊ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎች ነፃ የሕግ ድጋፍ የሚያገኙባቸውን ሁኔታዎች ማመቻቸት፣
◊ ለፍትህ ተቋማት የቀረቡ ጉዳዮች ሳይዘገዩ በአፋጣኝ እልባት የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
◊ በተለይ የማይዋዥቁና ሊተነበዩ የሚችሉ (Predictable) ውሳኔዎች ወዲያውኑ መስጠት የሚሉት ዋና ዋና ነጥቦች ትኩረት ሊሰጥባቸው ይገባል::

በአጠቃላይ በአንድ አገር ውስጥ የሕግ የበላይነት (the rule of law) መኖር መለኪያ ከሆኑት ነገሮች ውስጥ በተለይ ድጋፍ የሚሹ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ፍትሕ የማግኘት መብት ማረጋገጥ በወሳኝነት ሊታይ የሚገባው ነው:: እነዚህ የኅብረተሰብ ክፍሎች የህግ ስርአቱን እንዲያውቁት፣ እንዲጠቀሙበትና እንዲተማመኑበት ማድረግ ያስፈልጋል:: የሚጠበቅ ምክንያታዊና በቂ የሆነ ውሳኔ የሚሰጥ የፍትህ ተቋም መገንባት እንደዚሁም የዜጐችን በተለይ ደግሞ ድጋፍ የሚሹ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ፍትህ የማግኘት መብት ሊያስከብር የሚችል የፍትህ ስርአት እውን ማድረግ ለነገ የማይባል ተግባር ነው::

### *በአፓአፓ ድጋፍ ነፃ የህግ አገልግሎት የሚሰጡ ማእከላትና ዕድሮች ስምና አድራሻ*

**የማዕከሎች ስም**

◊ አዲስ አበባ - የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሕግ ፋኩልቲ የቀድሞ ተማሪዎች ማኅበር - አራዳ ምድብ ችሎት ቅጥር ግቢ - **011-1-579361**
◊ ድሬዳዋ - ብሩህ የሕግ ድጋፍ ለሚሹ ነፃ የሕግ አገልግሎት ማኅበር - የኢትዮጵያ ደረጃ መዳቢዎች ፎቅ ላይ - **025-1-123699**
◊ ሐረር - ሰላም የባለሙያዎች ማኅበር ለህዝብ - ሐረር ጠቅላይ ፍ/ቤት ፊት ለፊት ቴሌ ህንፃ ውስጥ - **025-6-665028**
◊ አዋሳ - ተስፋ የህግ ድጋፍ ሰጪ ማኅበር ለሕዝብ - አዋሳ ዙሪያ ወረዳ ፍ/ቤት ቅጥር ግቢ - **046-2-204163**
◊ ደሴ - የደሴ ከተማ ነፃ የህግ ድጋፍ መስጫ ማዕከል - ደሴ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ቅጥር ግቢ - **0331-123335**
◊ አዲስ አበባ - ቃሊቲ ማረሚያ ቤት ነፃ የህግ ድጋፍ መስጫ ማዕከል - **011-4-394900** /ተሃድሶ ክፍል/

**የዕድሮች ስም**

◊ አዲስ አበባ - የእድገት በኅብረት የልማት ማኅበር - አቃቂ ቴሌ ጀርባ - **091-1-355482**
◊ አዲስ አበባ - የአዲስ ፋና የግብይትና የወፍጮ አገልግሎት ሰጪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የኅብረት ሥራ ማኅበር የቀድሞ ቀበሌ ውስጥ - ፈረንሳይ ለጋሲዮን አካባቢ - **011-1-243619**
◊ ሐረር - አየለ ወርዶፋ መረዳጃ ዕድር - ቀበሌ 12 ቅጥር ግቢ - **025-6-660310**
◊ አዳማ/ናዝሬት/ - የአዳማ ከተማ ዕድሮች አጠቃላይ ማኅበር ጽ/ቤት - ዑመር ፎቅ ፊት ለፊት - **022-1-112999**
◊ ድሬዳዋ - እህትማማቾች ዕድር - አኮርድ የሰራው አዳራሽ ኬር ስኩዌርን ወረድ ብሎ - **025-1-120365**
◊ ባህር ዳር - የባህር ዳር ከተማ አጠቃላይ ዕድሮችና ጃምያዎች ህብረት - ቀበሌ 05 ቅጥር ግቢ - **058-2-207295**
◊ አዋሳ - የአዋሳ ከተማ አጠቃላይ እድር - 01/07 ቀበሌ ቅጥር ግቢ - **046-1-210436**
◊ ጅማ - የጅማ ከተማ ዕድሮች ኅብረት ለልማት ጽ/ቤት - ቀበሌ 5 አዳራሽ ግቢ ውስጥ - **047-1-119143**
◊ ደብረ ብርሃን - የ05 ቀበሌ የማርያም ዕድር- ቀበሌ 05 አዳራሽ ግቢ ውስጥ - **011-6-812755**
◊ አሰላ - የጭላሎ ተራራ ዕድር - **022-3311392**

# ፍትህ የማግኘት መብት በዝቅተኛ ኑሮ ከሚኖሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች አንፃር

APAP

ስድስት ኪሎ፣ወደ ዳግማዊ ምኒሊክ ሆስፒታል በሚወስደው መንገድ ፤
ያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤትን አለፍ ብሎ፣
አዲስ የተሰራው የቴሌኮሚዩኒኬሽን ህንፃ ፊት ለፊት

ፖ.ሣ.ቁ. 12484፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ስልክ 251-11-1243555፣ፋክስ 251-11-1243558
ኢ-ሜይል፡apap@ethionet.et
ዌብ ሳይት(ድረ-ገፅ): **http:**\\www.apapeth.org